**Hallo
Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ጤንነት

የጤንነት ስርዓት
የህክምና እና የአደጋ ኢንሹራንስ
ሕክምናዊ እንክብካቤ
እርግዝና / መውለድ
የአዕምሮ ጤንነት
በሞት ጊዜ

# የጤንነት ስርዓት

በስዊዘርላንድ ያለው የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በጣም የዳበረ ነው። ሁሉም ነዋሪዎች በአደጋ እና በህመም ላይ አጠቃላይ እና የግዴታ ዋስትናና ኢንሹራስ አላቸው። ብዙ የሕክምና ጣብያዎች፣ መድሃኒት ቤት እና ሆስፒታሎች አቅርቦቱን ያረጋግጣሉ።

## የኢንሹራንስ ስርዓት

በስዊዘርላንድ ሁሉም ነዋሪዎች ከአደጋ እና ከበሽታ ለመጠበቅ ሁሉም ኢንሹራንስ አላቸው። ወደዚህ አገር አዲስ የመጣ ማንኛውም ሰው ከገባ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ ኢንሹራንስ መግባት አለበት። ልጆች ከተወለዱ በሦስት ወር ውስጥ ኢንሹራንስ መግባት አለበት። የግዴታ ኢንሹራንስ ጥቅሞች በሕግ የተደነገጉ ናቸው። ሁሉም የመድን ዋስትና ወይም ኢንሹራንስ ያላቸው ሰዎች አንድ ዓይነት የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

## ፋይናንስ ማድረግ

የስዊዘርላንድ የጤና አጠባበቅ ስርዓት በመንግስት (የፌዴራል መንግስት፣ ካንቶኖች፣ የኮሙን ማዘጋጃ ቤቶች)፣ እና በግለሰቦች በጋራ በመተባበር ፋይናንስ የሚደርግ የሚሸፈን እና ፋናንስ የሚደረግ ነው። ግለሰቦች ለጤና መድን እና ለአደጋ መድን ወርሃዊ የኢንሹራንስ ድርሻቸውን ይከፍላሉ። ይህ በየአመቱ የሚዘጋጅ ሆኖ ከካንቶን ወደ ካንቶን ይለያያል። ማንኛውም ሰው ቢታመመ ወይም አደጋ ቢያጋጠመው ህክምና ወጪው (Franchise und Selbstbehalt) በመዋጮው መጋራት አለበት። ይሁን እንጂ ክፍያው ወይም ወጪው በዓመቱ ቢበዛ ከፍተኛ የክፍያ መጠን አለው ።

## የጽሑፍ ትርጉሞች

በውጭ ቋንቋ ከዶክተሮች፣ ፋርማሲስቶች ወይም ነርሶች ጋር መነጋገር በሚኖርበት ጊዜ ቀላል አይደለም። ስለዚህ አንዳንድ ሆስፒታሎች በልዩ የሰለጠኑ የባህል ተርጓሚዎች ነፃ ትርጉም ይሰጣሉ። ታካሚዎች ስለዚህ ጉዳይ እራሳቸውን አስቀድመው ማሳወቅ አለባቸው። ተርጓሚዎቹ ለዶክተር ወይም ለሌሎች ሁኔታዎች ጉብኝት ሊታዘዙ ወይም ሊቀጠሩ ወይም ሊጠሩ ይችላሉ። ግን ታድያ ሂሳቡን በራስዎ መክፈል አለብዎት።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/gesundheitssystem

# የህክምና እና የአደጋ ኢንሹራንስ

በስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው የአደጋ እና የጤና መድን ኢንሹራንስ ሊኖረው ይገባል። እነዚህ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በአደጋ፣ በህመም ወይም በእርግዝና ወቅት ወጪዎችን ይሸፍናሉ። ሁለቱም ዓይነት ኢንሹራንስዎች ወደ አገሪቱ ከገቡ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ባሉት ጊዜዎች ውስጥ መገባት

## የጤና እንክብካቤ ኢንሹራንስ (መሰረታዊ ኢንሹራንስ)

ሁሉም የስዊዘርላንድ ነዋሪዎች የጤና መድህን (መሰረታዊ ኢንሹራንስ፣ Grundversicherung) ራሳቸው የግድ መግባት አለባቸው። ወደ ስዊዘርላንድ ለመኖር አገር የሚቀይር ማንኛውም ሰው ይህን ለማድረግ ሦስት ወር አለው። በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው ቢታመም፣ ቢሆንም እንኳን ይሸፈናሉ። መሰረታዊ ኢንሹራንስ በብዙ የግል የጤና መድን አገልግሎት ሰጪዎች (Krankenkassen) ይሰጣል። የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎን ለመምረጥ ነፃ ነዎት። የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በስዊዘርላንድ የሚኖሩትን ሁሉ የመቀበል ግዴታ አለባቸው።
ኢንሹራንስ የገባ ሰው በየወሩ መክፈልል የሚገባውን ሂሳብ ይከፍላል። እነዚህ ፕሪሚየሞች እንደ ጤና ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እንደ ኢንሹራንስ ሞዴል ይለያያሉ። ስለዚህ ቅናሾቹን ማወዳደር ጠቃሚ ነው። ለሚቀጥለው ዓመት እስከ ህዳር መጨረሻ ድረስ የጤና መድን መቀየር ይችላሉ። መሰረታዊ ኢንሹራንስ ከታመሙ ወጪዎችን ብቻ ሳይሆን በእርግዝና እና ልጅ በመውለድ ጊዜም ጭምር ይከፍላል። የሚሰጡት አገልግሎቶች (ጥቅሞቹ) በሕግ የተደነገጉ ናቸው::
ማሳሰብያ፡ ለጥርስ ህክምና ወይም የመነጽር ወጪዎች አብዛኛውን ጊዜ በራስዎ መከፈል ወይም በፈቃደኝነት ተጨማሪ ኢንሹራንስ መግባት አለብዎት።

## የአደጋ ግዜ ኢንሹራንስ

ሰራተኞች በሳምንት ውስጥ ከ 8 ሰአታት በላይ የሚሰሩ ከሆነ በስራ ወቅት ለሚደርሱ አደጋዎች እና ነፃ ጊዜ በአሰሪው የኢንሹራንስ ዋስትና ይሰጣቸዋል። አነስተኛ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በትርፍ ጊዜያቸው ለአደጋ ዋስትና ወይም ኢንሹራንስ አይኖራቸውም እና በራሳቸውን የአደጋ ኢንሹራንስ መግባት አለባቸው። ይህ በግል ስራ የሚተዳደሩ እና ለሰራተኞች እና ስራ ለሌላቸው ሰዎች ሁሉም ይሠራል። ያልተቀጠሩ ሰዎች ከጤና ኢንሹራንስ ኩባንያቸው ጋር የአደጋ ኢንሹራንስ መውሰድ አለባቸው። የግል ተቀጣሪው ከሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጋር የአደጋ ኢንሹራንስ ሊወስድ ይችላል። የኢንሹራንሱ ክፍያ በየወሩ መክፈል ይኖርበታል። በሠራተኞች ላይ፣ በቀጥታ ከደመወዛቸው ላይ ይቀነሳሉ።

## የፕሪሚየም ቅነሳ

የጤና መድህን ፕሪሚየም መግባት የማይችሉ ሰዎች ለመሠረታዊ ኢንሹራንስ የፕሪሚየም ቅናሽ (Prämienverbilligung) ሊያገኙ ይችላሉ። ፕረምየም ለመቀበል አንድ ሰው የማመልከቻ ቅጽ ማቅረብ እና በንብረቶች እና ገቢዎች ላይ መረጃ መስጠት አለበት። ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ፣ ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ ፕረምየም ክፍያዎችን መክፈል ይጀምራል። የማህበራዊ መዋጮ ቢሮ (Amt für Sozialbeiträge) ስለ ፕረምየም ቅነሳ መረጃ ያቀርባል እና ምዝገባውን ይጀምራል።

## ከመሠረታዊ ኢንሹራንስ ላይ ሌላ ተጨማሪ ተጨማሪ ኢንሹራንስ

በግዴታ መገባት ካለባቸው መሰረታዊ ኢንሹራንስ በተጨማሪ የተለያዩ ማሟያ ኢንሹራንሶች (Zusatzversicherungen) በፈቃደኝነት መግባት ይችላሉ። እነዚህ በመሠረታዊ ኢንሹራንስ ያልተሸፈኑ እንደ የጥርስ ህክምና ያሉ ጥቅማ ጥቅሞችን ይሸፍናሉ። ተጨማሪ ኢንሹራንስ በሁሉም የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይሰጣል። የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎቹ ለአንድ ሰው ኢንሹራንስ እንዲገባ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በራሳቸው ሊወስኑ ይችላሉ እንዲሁም ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/kranken--und-unfallversicherung

# ሕክምናዊ እንክብካቤ

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ማንኛውም ሰው የታመመ ወይም አደጋ ያጋጠመው እንደሆነ መጀመሪያ የቤተሰብ ዶክተር ማየት ይኖርበታል ። በጥቃቅን በሽታዎች ወይም በአደጋዎች ጊዜ በመድሃኒት ቤት ውስጥ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ ። በጣም ከባድ በሆኑ ድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል መሄድ አለብዎት።

## መድሃኒት ቤቶች

መድሃኒት ቤቶቹ በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች (ያለ ሃኪም ትዕዛዝ የማይገዙ) እና ሌሎች መድኃኒቶችን ይሸጣሉ። ቀላል ሕመም ካለብዎት በመጀመሪያ ወደ መድሃኒት ቤት እንዲሄዱ ይመከራል። ፋርማሲስቶቹ በደንብ የሰለጠኑ ናቸው እና ደንበኞቻቸውንም ያማክራሉ፣ በፔተርስግራበን 3 (Petersgraben 3 ) የሚገኘው የድንገተኛ መድሃኒት ቤት በሌሊት እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ ክፍት ስለሆነ በድንገተኛ ጊዜ መድሃኒት ማግኘት ይችላሉ።

## የቤተሰብ ዶክተር / የሕፃናት ሐኪም

በስዊዘርላንድ ብዙ ሰዎች የቤተሰብ ዶክተር (Hausarzt oder Hausärztin) አላቸው። ሃኪሞቹ የግል የሕክምና ታሪክን ያውቃሉ እና ለህክምና ችግሮች የመጀመሪያ የመገናኛ ተጠሪዎች ናቸው። ለልጆች የሕፃናት ሐኪሞች አሉ። አስፈላጊ ከሆነ ታካሚውን ወደ ልዩ ባለሙያ ሐኪም ወይም ወደ ሆስፒታል ይልካሉ ። ከባድ ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠመ ብቻ ነው ወደ ሆስፒታል በቀጥታ መሄድ ያለብዎት። ለሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች የህክምና ድንገተኛ የጥሪ ማእከል (Medizinische Notrufzentrale፣ MNZ) ከዶክተር ቢሮ የስራ ሰዓት ውጭ ይገኛል። ይህም በቀን 24 ሰዓት በ061 261 15 15 ደውለው በድንገተኛ አደጋ ውስጥ ላሉ ህፃናት እና ወጣቶች የህጻናት ህክምና አገልግሎት ከተከፈቱበት ሰዓት ውጪ የሜድጌት ኪድስ መስመር በክፍያ በሚደወል ስልክ ቁጥር 0900 11 44 11 ማግኘት ይቻላል።11 ማግኘት ይቻላል።

## የጥርስ ሐኪም

የጥርስ ህክምናን ወጪ አብዛኛውን ጊዜ በግልዎ መከፈል አለብዎት። ሆኖም ግን የጥርስ ህክምናን የሚሸፍን ተጨማሪ ኢንሹራንስ_የመግባት አማራጭ አለ። በትምህርት ገበታ የሚገኙ ልጆች፣ በዓመት አንድ ጊዜ ነጻ የጥርስ ምርመራ የማግኘት መብት አላቸው። ትምህርት ቤቱ በዚህ ላይ አስፈላጊ መረጃ ይሰጣል።

## Krankenhaus / የአደጋ ጊዜ ጣቢያዎች (DE)

አንድ ሰው ወደ ሆስፒታል (Spital) መሄድ ካለበት፣ ብዙውን ጊዜ በዶክተር ይመዘገባል። አንድ ሰው በቀጥታ ወደ ሆስፒታል ድንገተኛ ጣቢያ መሄድ ያለበት ለየት ያለ ከባድ ድንገተኛ አደጋዎች ካጋጠሙት ብቻ ነው። ሁኔታው ለሕይወት አስጊ ከሆነ ወይም በሽተኛው ወደ ህክምና መወሰድ ካለበት የአደጋ ጊዜ ቁጥር 144 መደወል አለበት። ቀላል በሆኑ ድንገተኛ አደጋዎች አጠቃላይ ህክምናውን የሚመለከተው ሀኪሙ ነው።

## እቤት ውስጥ መንከባከብ

ቤት ውስጥ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የታመሙ ሰዎች ወይም እንክብካቤ የሚፈልጉ ሰዎች የሆስፒታል ያልሆነ ነርሲንግ (Spitex) አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላሉ። ስፔሻሊስቶች በሽተኞቹን ለመንከባከብ ወይም በቤቱ ውስጥ ለመርዳት ወደ ህሙማኑ ቤት ይሄዳሉ። ይህ አቅርቦት በህመም፣ በአደጋ፣ በእርጅና፣ በእርግዝና ወቅት ወይም ከወሊድ በኋላ በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት በድጋፍ ላይ ጥገኛ ለሆኑ ሰዎች ነው። አንዳንድ ወጪዎች በመሠረታዊ ኢንሹራንስ (Grundversicherung) የተሸፈኑ ናቸው. ከSpitex Basel በተጨማሪ ብዙ የግል Spitex አቅራቢዎች አሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/medizinische-versorgung

# እርግዝና / መውለድ

ነፍሰ ጡር ሴቶች ለአስፈላጊ ምርመራ ምንም ገንዘብ መክፈል የለባቸውም። የወሊድ ወጭዎችም በሙሉ በመሠረታዊ ኢንሹራንስ ይሸፈናሉ። ወላጆች ከወሊድ በፊት እና በኋላ ነፃ ምክር ሊያገኙ ይችላሉ።

## አገልግሎቶች እርግዝና / መውለድ

ከእርግዝና ወይም ወሊድ ጋር የተያያዙ የሕክምና አገልግሎቶች በመሠረታዊ ኢንሹራንስ (Grundversicherung) የተሸፈኑ ናቸው። ይህም ከመውለዱ በፊት መደበኛ ምርመራዎችን፣ በወሊድ ጊዜ እና አስፈላጊውን እንክብካቤን ከወሊድ በኋላ ያካትታል። ነፍሰ ጡር ሴቶች ገና በመጀመርያ ደረጃ ዶክተር ወይም አዋላጅ ማማከር አለባቸው። ሆስፒታሎች እና አዋላጆችም የወሊድ ዝግጅት ኮርሶችን ይሰጣሉ (Geburtsvorbereitungskurse)። ለስደተኞች ልዩ ኮርሶች አሉ። የማዋለድ ሂደቱ በሆስፒታል ውስጥ፣ በወሊድ ማእከል ወይም በቤት ውስጥ ሊከናወን ይችላል።

## ከወሊድ በኋላ

በስዊዘርላንድ ውስጥ ወላጆች ከወሊድ በኋላ ምክር መፈለግ የተለመደ ነው። ለዛ ነው የወላጆች ምክር መስጫ ጣብያ (Elternberatungsstelle) ያለው። ይህ ስለ ሕፃኑ እድገት፣ አመጋገብ እና እንክብካቤ መረጃ ይሰጣል። የሚሰጡት የምክር አገልግሎቶች ነፃ ናቸው። ሐኪሙ ወይም አዋላጅ ለእናቲቱ እና ለህፃኑ አስፈላጊ የሆኑትን የክትትል ምርመራዎች ያሳውቅዎታል። ህጻኑ ከተወለደ ከሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ (መሠረታዊ ኢንሹራንስ, የአደጋ መድን ኢንሹራንስ ) ለህመም እና ለአደጋዎች ዋስትና መግባት በጣም አስፈላጊ ነው ። ከመውለድዎ በፊት ይህን ማድረግ ጥሩ ነው።

## ክትባት

ህጻናት በቶሎ በጊዜ ከተወሰኑ በሽታዎች እንዲከተቡ ይመከራል። ይሁን እንጂ ክትባቶች አስገዳጅ አይደሉም። ለታዘዙት ክትባቶች ወጪዎች ብዙውን ጊዜ በመሠረታዊ ኢንሹራንስ ይሸፈናሉ። የሕፃናት ሐኪም ወይም የወላጅ ምክር ማእከል ክትባቶችን በሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ።

## ፅንስ ማስወረድ

በስዊዘርላንድ በመጀመሪያዎቹ 3 ወራት እርግዝና ፅንስ ማስወረድ ይፈቀዳል። ከ12 ኛው ሳምንት እርግዝና በኋላ ፅንስ ማስወረድ የሚቻለው የሴቲቱ አካላዊ እና / ወይም አእምሮአዊ ጤንነት አደጋ ላይ ከሆነ ብቻ ነው። ሐኪሙ ይህንን አደጋ እንዳለ መገምገም አለበት። ፅንስ ማስወረድ የሚያስብ ማንኛውም ሰው ነፃ ምክር የማግኘት መብት አለው። ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ወጣት ሴቶች ልዩ የምክር አገልግሎት ማእከልን ማነጋገር አለባቸው። የሁሉም የሕክምና አገልግሎቶች ወጪዎች በመሠረታዊ ኢንሹራንስ ይሸፈናሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/schwangerschaft--geburt

# የአዕምሮ ጤንነት

በስዊዘርላንድ ውስጥ በአእምሮ እና በአካል በሽታዎች መካከል ምንም ልዩነት የለም። መሰረታዊ ኢንሹራንስ የአእምሮ ሕመምተኞችን በልዩ ባለሙያዎች ለማከም እና ለሆስፒታል ቆይታ ይከፍላል።

## ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት

በስዊዘርላንድ ውስጥ በአስቸጋሪ የግል እና የቤተሰብ ሁኔታዎች ውስጥ ሊረዱዎት የሚችሉ ብዙ ልዩ ባለሙያዎች አሉ። መሰረታዊ ኢንሹራንስ (Grundversicherung) የአእምሮ ሕመሞችን ለማከም ህጋዊ እውቅና ባላቸው እንደ ሳይካትሪስቶች ባሉ ባለሙያዎች የሚደረግ ምርመራ ይከፍላል። የሆስፒታል ቆይታም ጭምር ይከፈላል። ችግሮች ካጋጠሙዎት ወደ ታዋቂ ያልሆኑ የምክር ማእከላት ያለክፍያ መሄድም ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አቅርቦቶቹ በስልክ፣ በኢሜል ወይም በቻት (ስልክ 143፣ www.143.ch) የምክር አገልግሎት ማግኘት ይቻላል። ነገር ግን በቤተሰብ ዶክተር (Hausärztin oder der Hausarzt) ዕርዳታ ማግኘት ይቻላል። አንድ ሰው እራሱንም ሆነ ሌሎችን የመጉዳት ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ከገባ በፍጥነት እርምጃ መወሰድ አለበት። በእንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ የፖሊስ እርዳታ ማግኘት ይቻላል። (ስልክ 117)

## ህፃናት ልጆች እና ወጣቶች

የአእምሮ ጤና ችግር ላለባቸው ለጎረምሳ ወጣቶች ነፃ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂካል አገልግሎት (Schulpsychologischer Dienst) ጥሩ የመጀመሪያ ደረጃ መሄጃ ቦታ ነው። ስለ ልጆቻቸው የሚጨነቁ ወላጆችም እዚያ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የህፃናት የድንገተኛ አደጋ የስልክ መስመር ለህፃናት እና ለወጣቶች በስልክ፣ በኢሜል ወይም በቻት (ስልክ 147፣ www.147.ch) ለህጻናት እና ጎረምሶች የስነ-አእምሮ ድንገተኛ አደጋዎች, ወላጆች የልጆች እና የጉርምስና የአእምሮ ህክምና (Kinder- und Jugendpsychiatrie) በስልክ ቁጥር 061 325 51 00 ማግኘት ይችላሉ።

## የሱስ በሽታ

የሱስ እርዳታ በባዝል ክልል (Suchthilfe Region Basel) እና የሁለቱም ባዝል የመድብለ ባህላዊ ሱስ ምክር ማእከል (Multikulturelle Suchtberatungsstelle, MUSUB) ሱሶኞችን ይረዳሉ። ኤጀንሲዎቹ ነፃ ሚስጥራዊ ምክር እና ድጋፍ ይሰጣሉ። ስለ ዘመዶችዎ ወይም ስለ እርስዎ ቅርብ ሰዎች የሚጨነቁ ከሆነ የምክር ማእከሎችን ማነጋገር ይችላሉ። በተጨማሪም በአንዳንድ የውጭ ቋንቋዎች ምክር ይሰጣሉ። ሱስ በአልኮል ወይም በአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነት ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የሱስ መማክርት ማዕከላት እንደ የቁማር ሱስ፣ የግዢ ሱስ ወይም የኢንተርኔት ሱስ እና የአመጋገብ ችግሮች ካሉ ሌሎች ሱሶች እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። ጥያቄዎች በኢሜል ጭምር ሊጠየቁ ይችላሉ።

## መንፈሳዊ ጉዳት /ትራውማ

በሕይወታቸው ውስጥ መጥፎ ነገር ያጋጠማቸው እና ይህም ተፅእኖ ያደረባቸው ሰዎች ድጋፍ መፈለግ አለባቸው። ምክንያቱም የስሜቶች መቃወስ ከባድ የአእምሮ ሕመሞች ናቸው። ከሥነ ልቦናዊ ችግሮች እና ሕመሞች የምክር እና የድጋፍ አገልግሎቶች በተጨማሪ በጦርነት እና በማሰቃየት ለተጎዱ ልዩ የመገናኛ ማእከላት እና ህክምናዎች አሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/psychische-gesundheit

# በሞት ጊዜ

ከቤተሰብዎ ውስጥ አንድ ሰው ከሞተ ለሚመለከተው ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ አለብዎት። ከፈለጉ፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ የቀብር ስነስርዓት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ጋር ይደውላል። የቀብር ሥነ ሥርዓት አስፈፃሚው ድርጅት አስከሬኑን ወደ መቃብር ወይም ወደ ውጭ አገር ያጓጉዛል።

## ሞትን ማመልከት/ማስታወቅ

ከቤተሰብዎ ውስጥ አንድ ሰው ከሞተ፣ ሐኪም የሞት የምስክር ወረቀት ፎርም መሙላት አለበት። ከዚያ በኋላ፣ ሞቱን ለባዝል- ከተማ Basel-Stadt መዝገብ ቤት ማሳወቅ አለብዎት።

ሟቹ በሆስፒታል፣ በጡረታ ቤት ወይም በአረጋውያን መንከባከቢያ ውስጥ ቢሞት፡-

• የሆስፒታሉ ወይም የአረጋውያን መንከባከቢያው አስተዳዳሪ መሞቱን ለመዝጋቢ ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት።

ሰውዬው ሌላ ቦታ ከሞተ፡-

• እርሶ እንደ ዘመድ፣ ሞትን ለባዝል-ከተማ ካንቶን Basel-Stadt መዝገብ ቤት ማሳወቅ አለብዎት።

በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ነጻ ቀብር ወይም ሬሳው ከተቃጠለ አመዱ ነፃ ቀብር ያገኛል።

## ወደ ውጭ አገር መመለስ/ማሰናበት

በባዝል-ከተማ ካንቶን Basel-Stadt ውስጥ ከቤተሰብዎ የሆነ ሰው ሞቶ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን የእርስዎ ፍላጎት ሟቹ ውጭ አገር እንዲቀበር ነው። የተፈቀደለት የቀብር ስነስርዓት ፈፃሚ ድርጅት ለዚህ ፕሮቶኮል ማሟላት አለበት። ፕሮቶኮሉ "የሬሳ ሳጥን እና ማሸግያ ፕሮቶኮል" ይባላል። ዋናውን ፕሮቶኮል ለBasel-Stadt ካንቶን የቀብር ስነስራዓት አስፈፃሚ ማሳየት አለብዎት። ከዚያም የቀብር ስነስራዓት አስፈፃሚ ድርጅቱ የሞት የምስክር ወረቀት ይሰጣል። በእነዚህ ሰነዶች ብቻ ቀባሪው አስከሬን እንዲቀበር ወደ ውጭ አገር መቃብር ማጓጓዝ ይችላል። እርስዎ፣ የቤተሰብ አባል እንደመሆንዎ መጠን፣ ወጪውን መክፈል አለብዎት።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gesundheit/death